INTERME

በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን
አዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ማ/ቅ/ጽ/ቤት
EHTIOPIAN REVENUE AND CUSTOMS AUTHORITY
A.A. KAIITY CUSTOMS BRANCH OFFICE

የውስጥመጻጻፊ

ቁጥር፡ ም/ሥ/ጉ/ጉ/036/11
ቀን፡ 10/03/2011

- ለ፡ ጉ/ስ/ስ/አፈፃፀም የስራ ሂደት
- ለ፡ ድህረ ዕቃ አወጣጥ ቡድን
- ለ፡ ጉምሩክ ጉዳዮች አቤቱታ አጣሪ ፅ/ቤት
- ለ፡ ህግ ማስከበር የስራ ሂደት
- ለ፡ ገላን ተርሚናል ማ/ጽ/ቤት

- ከ፡ ም/ስራ አስኪያኪያጅ /ጉምሩክ ጉዳዮች/
አዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

የጉምሩክ ኮሚሽን በደብዳቤ ቁጥር 4.0/112/11 በቀን 06/03/2011 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ የአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት በቁጥር አቃጉ02/አ51/78 በ19/01/2011 በተፃፈ ደብዳቤ ከኢንቨስትመንት ኮሚሽን በተፃፈ ደብዳቤ አማካኝነት ከተሽከርካሪ ጋር ተገጥሞ የሚመጣ Carry Boy ቀረጥ እንዲከፈልበት የወሰነ ስለሆነ በምን አግባብ ቀረጥና ታክስ መከፈል እንዳለበት እና ከኢንቨስትመንት ውጪ የቀረጥ ነፃ መብት ያላቸው ግለሰቦች Carry Boy ያላቸው ተሽከርካሪ ሲያስገቡ በምን ሁኔታ መስተናገድ እንዳለባቸው ውሳኔ እንዲሰጥበት መጠየቁን ገልፆ አብሮ የሚመጣ Carry Boy ጊዜያዊ ውሳኔ የተሰጠበት ስለሆነ በውሳኔው መሰረት እንዲስተናገድ እያሳሰብኩ የተላከውን ውሳኔ 2 ገፅ ደብዳቤ አያይዘን ልከናል፡፡

ከሰላምታ ጋር

ግልባጭ፣

- ለስራ አስኪያጅ ጽ/ቤት
- ለጉ/ስ/ስ/አፈፃፀም የስራ ሂደት
አዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Revenues
Customs Commission

06 2011
ሐ-0/11/2/11

የጉምሩክ ስነ-ስርዓት ለሚፈፀምባቸዉ ቅ/ጽ/ቤቶች

<u>በያሉበት</u>

ጉዳዩ:- <u>ከፒክ-አፕ ተሽከርካሪዎች ጋር ወደ አገር የሚገባ የኋላ ኮፈን (Carry Boy) ይመለከታል</u>::

የአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት በቁጥር አቃጉ02/አ51/78 በ19/01/2011 በተጻፈ ደብዳቤ ከኢንቨስት ኮሚሽን በተጻፈ ደብዳቤ አማካኝነት ከተሽከርካሪ ጋር ተገጥሞ የሚመጣ Carry Boy ቀረጥ እንዲከፈልበት የወሰነ ስለሆነ በምን አግባብ ቀረጥና ታክስ መከፈል እንዳለበት እና ከኢንቨስትመንት ዉጪ የቀረጥ ነጻ መብት ያላቸዉ ግለሰቦች Carry Boy ያላቸዉ ተሽከርካሪ ሲያስገቡ በምን ሁኔታ መስተናገድ እንዳለባቸዉ ዉሳኔ እንዲሰጥበት ጠይቋል::

በመሆኑም Carry Boy ከዓለምአቀፍ የታሪፍ አመዳደብ ህግ አንጻር የተሽከርካሪዉ ተጨማሪ አካል ስለሆነ ወደ አገር ለገባዉ ፒክ አፕ ተሽከርካሪ የሚሆንና የሚገጥም እስከሆነ ድረስ ከተሽከርካሪዉ ሳይነጠል የተሽከርካሪዉ ተጨማሪ አካል ሆኖ ለብቻዉ የተለየ የታሪፍ ቁጥር ሳያስፈልገዉ በአንድ ታሪፍ ቁጥር ላይ አብሮ የሚመደብ ይሆናል:: ሆኖም በኢንቨስትመንት ኮሚሽን በኩል ኢንቨስተሮች ፒክ አፕ ተሽከርካሪ በቀረጥ ነጻ እንዲያስገቡ ሲፈቅድ Carry Boy አብረዉ ካስገቡ ቀረጥ እንዲከፍሉበት በመወሰኑ ምክንያት በአጠቃላይ የዚህ እቃ መስተንግዶ እና በጉምሩክ መረጃ አያያዝ ላይ ችግር እየፈጠረ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል:: ይሁንና በኢንቨስትመት ኮሚሽን በኩል Carry Boy ያላቸዉ ፒክ አፕ ተሽከርካሪዎች ከCarry Boy ጋር በአንድ የታሪፍ ቁጥር እየተመደቡ መስተናገድ ሲገባቸዉ በCarry Boy ቀረጥ ይከፈለበት ተብሎ የተወሰነዉ ላይ በእኛ በኩል ከኢንቨስትመት ኮሚሽን ጋር በመወያየት ዘላቂ መፍትሔ እስከሚቀመጥለት ድረስ ከፒክ አፕ ተሽከርካሪዎች ጋር አብሮ የሚመጣ Carry Boy መስተንግዶ በሚከተለዉ መልክ እንዲሆን ጊዜያዊ ዉሳኔ ተሰጥቶበታል::

1. የኢንቨስትመንት ኮሚሽን ለኢንቨስተሮች ፒክ አፕ ተሽከርካሪዎች ከቀረጥ ነጻ ሲፈቅድ ከኋላ ከፊት (Carry Boy) ጋር መሆኑን በግለጽ ከጠቀሰ አብሮ የመጣዉ Carry Boy ለመጣዉ ተሽከርካሪ የሚሆን መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ ተሽከርካሪዉ በሚመደብበት ታሪፍ ቁጥር ላይ እንደ አንድ የተሽከርካሪዉ አካል ተወስዶ እንዲመደብና ከተሽከርካሪዉ ጋር በቀረጥ ነጻ እንዲስተናገድ፣
2. የኢንቨስትመንት ኮሚሽን ለኢንቨስተሮች ፒክ አፕ ተሽከርካሪዎች ከቀረጥ ነጻ ሲፈቅድ Carry Boy የሚያካትት መሆኑን በግልጽ ካልጠቀሰና በቀረጥ ነጻ ከተፈቀዳዉ ፒክ አፕ ተሽከርካሪ ጋር አብሮ የመጣ Carry Boy ከተሽከርካሪዉ ተነጥሎ ለብቻዉ ወይም ለዚህ ዉሳኔ ሲባል የተሽከርካሪዉ አካል እንዳልሆነ ታሳቢ በማድረግ በታሪፍ አመዳደብ ህግ መሰረት በሚመለከተዉ የታሪፍ ቁጥር ላይ ተመድቦ ተገቢዉ ቀረጥና ታክስ እንዲሰበሰብበት እንዲደረግ፣
3. ለኢንቨስትመንት በቀረጥ ነጻ ከሚፈቅዱት ፒክ አፕ ተሽከርካሪዎች ዉጪ በተለያዩ የህግ መሰረቶች ለግለሰቦችና ለድርጅቶች በቀረጥ ነጻ ከሚፈቀዱ ፒክ አፕ ተሽከርካሪዎች ጋር አብሮ የሚገባ Carry Boy ለገባዉ ተሽከርካሪ የሚገጥም ወይም ተስማሚ መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ ከCarry Boy ላይ ቀረጥ ለመሰብሰብ የሚያስችል የህግ መሠረት አለመኖሩን በመገንዘብና እቃዉ የተሽከርካሪዉ ተጨማሪ አካል ሆኖ ስለሚወሰድ ከተሽከርካሪዉ ጋር አብሮ ተመድቦ ቀረጥና ታክስ ነጻ ሆኖ እንዲስተናገድ፣
4. ከንግድ አላማ ዉጪ ፒክ አፕ ተሽከርካሪ ቀረጥና ታክስ ከፍለዉ በስማቸዉ እንዲያስገቡ የተፈቀደላቸዉ ግለሰቦች እና ድርጅቶች ለተሽከርካሪዉ የሚሆን Carry Boy አብረዉ ሲያስገቡ ኬሪቦዩ ተሽከረካሪዉ በሚመደብበት ታሪፍ ቁጥር አብሮ ተመድቦ እንደ አንድ የተሽከርካሪዉ ተጨማሪ አካል ተወስዶ ቀረጥና ታክሱ እንዲሰበሰብ የተወሰነ ሲሆን ይህን ጊዜያዉ ዉሳኔ በጥብቅ ዲሲፕሊን ተግባራዊ እንዲደረግ ያስተላለፍን መሆኑን እንገልጻለን።

ከሠላምታ ጋር

ደበሌ ቃበታ ሁርሳ
የጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነር

ግልባጭ:-

- ለዋጋ ትመናና ታሪፍ ምደባ አሠራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለጉምሩክ አሠራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለአምራችና ወጪ ንግድ ድጋፍ ዳይሬክቶሬት

ገቢዎች ሚኒስቴር